# ለኣቶ ተረፈ ወርቁ  የተሰጠ ኣስተያየት

ገብረ ሥላሴ ኣርኣያ

መጋቢት 2010 ዓ/ም

ኣቶ ተረፈ ወርቁ የተባሉ ኣንድ ኣስተያየት ሰጪ ከበጎ ኣስተሳሰብ የሚመነጭ ጥያቄ ኣዘል ቁጭታቸውን "ኢትዮጵያዊ ብሔራዊ ጀግናችን ማን ነው" በሚል ኣርእስት ዓይጋፎርም ድህረ ገፅ ላይ ኣንድ ጽሁፍ ኣስነብበውናል። ጸሃፊው ቁጭታቸውን ሲገልጹ:

*"በቀደሙ የሀገራችን የታሪክ ፈርጦችና ጀግኖቻችን ላይ አንዳች ስምምነት የሌለን ወደመሆን የመጣን ሁላችንም እንደ አገርም ሆነ እንደ ሕዝብ ይወክለናል የምንለው ብሔራዊ ጀግና አልባ፣ የአንድነታችን፣ የነጻነታችንና የልዑላዊነታችን ምልክት የሚሆነን ብሔራዊ ጀግናችንን በስምምነት ለመመረጥም ሆነ ለመወሰን ተለያየና የተከፋፈለ ልብ ያለን ሕዝቦች ኾነናል፡፡"* በማለት ለዚች ኣገር የኩራት ምንጭ የሆኑ ከቋራው ካሣ ወይም ኣጼ ቴድሮስ እስከ ኣጼ ሃይለ ሥላሴ የነበሩትን ነገስታት በመጥቀስ በእነሱ እና በታሪካችን ላይ ያለን ያለመስምማት እንደሚያሳዝናቸው ይገልፃሉ።

ለዚሁም *"ባለፈው ሩብ ክፍለ ዘመንም በሀገራችን የተዘረጋው የብሔር ፖለቲካና በሥልጣን ላይ ያለው መንግሥትም በሕዝብ ዘንድ ያለውን ቅቡልነት ለማረጋገጥ በሚያደርገው ያላሰለሰ ጥረት የቀድሞ ሥርዓትና መሪዎች በሀገሪቱ ታሪክና በሕዝቡ ሕይወት ውስጥ የነበራቸውን ሚና እና ኣስተዋፅዖ በብዙ መንገድ እንዲሸረሸር አድርጓል፡፡ በዚህም ምክንያት በአብዛኛው የኅብረተሰብ ክፍል ዘንድ በሀገሪቱ ታሪክ የቀድሞ መሪዎች ዙሪያ የጋራ መግባባት እንዳይኖርን ሆነናል፡፡"* በማለት ስርኣቱን ተጠያቂ ያደርጉታል።

ጸሃፊው ባነሱት ጉዳይ ላይ፣ ማለትም ብሄራዊ ጀግኖቻችንን በማክበርና በታሪካችን ላይ ስምምነት መፈጠር በሚለው ህሰባቸው ሙሉ በሙሉ እስማማለሁ። ሆኖም ላለመስማማት ያበቁንን ዋና ዋና ምክንያቶች በመፈረጅ ላይ ልዩነት ስላለኝ በዚህ ዙሪያ መልእክቴን ለማስተላለፍ እሞክራለሁ።

በእኔ እምነት ለእንደዚህ ኣይነት ያለመግባባት የደረስንበት ዋና ምክንያት ጸሃፊው እንደገለጹት ባለፈው ሩብ ክፍለ ዘመን ወይም በዘመነ ኢህኣዴግ በተፈጠረው የፖለቲካ ስርኣት እና ክልሎች መፈጠር ኣይደለም። ኣዲሱ የፌደራል ስርኣት ያመጣው ራስን የማስተዳደር መልካም እድል እንደተጠበቀ ሆኖ በፌደራሊዝም ላይ ያለን የተዛባ ትርጉም የራሱ የሆነ ኣሉታዊ ኣስትዋፅኦ ያደረገ ቢሆንም ያለፉት መሪዎች በማሳነስ ወይም በማግዘፍ ላይ ግን ይህ ነው የሚባል ኣስተዋፅኦ የለውም። እንዲህ ኣይነት ቁንጽል የሆነ ትርጉም ማስያዝ ታሪካችንን ያለመረዳት (የጸሃፊው የታሪክ ግንዛቤ ባላውቅም) ኣሊያም እውነቱን ለመስማት ዝግጁ ካለመሆን የሚመነጭ ነው የሚመስለኝ። ዋናው ችግሩ እዚህ ላይ ነው ያለው። ያለፍንበትን ታሪክ በነፃነት ለመናገርና ለመፃፍ ለመጀመጀመሪያ ጊዜ ሊባል በሚችል ሁኔታ መብት ያገኘንበት ኣሁን ባለው ስርኣት በመሆኑ ካሁን ቀደም ያልተነገረው ነገር ፈጥጦ ሊወጣ ችለዋል። በዚህ ሂደት ኣንዱ ያለፈውን ህመሙን ተገቢና ተገቢ ባልሆነ ሁኔታ ለመግልጽ ሲሞክር፣ ሌላው ደግሞ እውነቱን ሳንደባበቅ ተነጋግረን ጽፈን እና ለደረሰው ግፍም እውቅና ተሰጣጥተን ለትውልዶች መማሪያ ይሁን ሲል፣ በተቃራኒውም ደግሞ የደረሰ ግፍና መነጠል የለም፣ ምናልባት ካለም ለኣገር ኣንድነት ሲባል የተፈጸመ ሊሆን ይችላል፣ የጀግኖቻችን ስም ማጥፋት ነው ከማለት ኣልፎ እንዲህ ኣይነት ነቀፌታ ለሚያነሱ ዜጎች የብሄራቸውን ስም እየተጠራ ከሃዲና

ያነሰ ኢትዮጵያዊ ኣድርጎ በመሳል ከራዲዮ እስከ ቴሌቪዥን፣ ከመፃህፍት እስከ ቪድዮ ፊልሞችን በማምረት የማያቋርጥ የጥላቻና ከፋፋይ ዘመቻ በማካሄድ ልዩነቱን በከፍተኛ ደረጃ ሊያጦዙት ችለዋል። በግንኙነታችን እና ለታሪካችንም ሆነ መሪዎቻችን ያለን እይታ ከዚህ የተዛባ የኣረዳድና እምነት ችግር የሚመነጭ ነው።

እውነቱን እንነጋገር ከተባለ፣ የብሄር ፖለቲካ የተፈጠረው ጸሃፊው እንዳሉት ከደርግ ውድቀ ማገስት ሳይሆን ከዓድዋ ጦርነት ማግስት ኣጼ ሚኒሊክ የተከተሉት የኣግላይ ጠቅላይ የፖለቲካ ስርኣት የወለደው መሆኑን ግልጽ ማድረግ ተገቢ ነው። የዓድዋ ድል ከጫፍ እስከ ጫፍ የነበሩ ኢትዮጵያዊያን ብሄርብሄረ ሰቦች የተገኘ ድል እንደነበረ ተረስቶ በሌሎች ብሄር ብሄረሰቦች ላይ የሸዋ ልእልናን በማረጋገጥ የተጠናቀቀ እንደነበር የታሪክ መዛግብት ያስረዳሉ። ለዚህ ማሳያ የሚሆነው ከትግራይ እስከ እስከ ሃረርጌ፣ ባሌ፣ ደቡብ፣ ወለጋ እና ከፋ ያለውን የኢትዮጵያ ግዛታቸው የኣንድን ብሄር የበላይነት የሚያሳይ ሹመኞችን በማስቀመጥ የኣካባቢውን ብሄር ተወላጆች (በጊዜው የነበሩ መሳፍንቶች) ወደ ዳር ገፈተዋል ወይም በጉልበት ኣስወገደዋል። እንዲያውም ኣንዳንድ ክፍለ ሃገርማ (ባሌ፣ ኦጋዴን፣ ከፋ፣ ጋምቤላ መቱ ኤሊባቡር እና ደቡብ ህዝቦችን) ከኢትዮጵያዊው ይልቅ ፈረንጅ ታማኝ ሆኖላቸው የኣካባብዊን ሰው በማስወገድ ሩሲያዊ ፣ ጣሊያንዊ፣ ፈረንሳያዊ ኣስተዳዳሪዎች እና ኣማካሪዎች እንደሾሙ የታሪክ መዛግብቶች ያወሳሉ። ይሄንን ኣይነት ስርኣት ባልተቀበሉ ህዝቦች ከትግራይ እስከ ደቡብ እና ምስራቅ ኢትዮጵያ የተወሰዱ ጭካኔ የተሞላባቸው ጭፍጨፋዎች በታሪክ ሰነዶች ሰፍረዋል። ከኣጼ ሚኒሊክ ቀጥለው የመጡት ኣጼ ሃይለ ሥላሴም የነበረውን የጠቅላይ ኣግላይ የፖለቲካ ስርኣት በከፋ እና እጅግ በረቀቀ ተንኮል ኣላብሰው ኣስቀጥለውታል። “እኛን መስላቹ ንሩ” በሚል ፖሊሲ ኣንድ ቋንቋ፣ ኣንድ ሃይማኖትና ማንነት በማልበስ ሙሉ ኢትዮጵያዊ ማድረግ ተግባር ተፈጽመዋል። የልማት ጥያቄ የጠየቁ ህዝቦች እኮ ኣማርኛ ሳትችሉ የሚሰጥ ነገር የለም ነበር የተባሉት።

ሌላው እስቲ በታሪካችን ላይ ከማያስማሙን ካላዋቸው ጉዳዮዮ ጥቂቶችን እናንሳ። ጸሃፊው እንዳስቀመጡት ዐፄ ምኒልክ *“ለአፍሪካና ለመላው ጥቁር ሕዝብ ነጻነት ፋና ወጊ እንዳልሆኑ ሁሉ በሚሊዮን የሚቆጠሩ የኦሮሞና ሌሎች ሕዝቦችን የጨፈጨፉና ያስጨፈጨፉ ንጉሥ/መሪ መሆናቸውን ነው አንዳንዶች የሚከራከሩት፡፡”* ይሉናል። ይህ ኣባባል ግዙፍ ችግር ኣለበት። ሲጀምር የኣድዋው ጦርነት ድል “ፋና ወጊ” (ጀማሪ፣ ቀዳሚ) ኣይደለም። ከዚህ ጦርነት በፊት ኢትዮጵያዊያን ከውጭ ወራሪዎች ጋር 13 ትልልቅ ውጊያዎች ገጥመው በድል ተወጥተዋል። እነዚህ ጦርነቶች እና የተገኙት ድሎች በኢትዮጵያዊያን ዘንድ የታሪክ እና የሉኣላዊነት ስነልቦና ፅኑ መሰረት ሊፈጥሩ ያስቻሉና ለዓድዋው ጦርነትም ስንቅ እና ፋና ወጊ ሆነው ያገለገሉ ናቸው። በኣጭሩ የዓድዋ ድል የፊተኞቹ ድሎች ቅጥያ እንጂ የመጀመሪያው ኣይደለም። ኣውሮፓዊያን፣ ግብጾች፣ ሱዳኖች እና ቱርኮች በጥቁር ኣፍሪካውያን መሪውችና ሰራዊት ደጋግመው እንደተሸነፉና ኣገራቸውን በነፃነት ሳይሸራርፉ እንዳስቀጠሉ የታሪክ ስነዶች ያስረዳሉ። ከጦርነቱ በፊትና በወቅቱ የነበረ የAugustus B. Wylde (1901), ቀደም ብሎ የመጣው እንግሊዛዊው ልዑክ Gerald Portal (1892) እና የታሪክ ተማራማሪው Sven Rubenson (1976) ከብዙዎቹ ጥቂቶቹ በፃፉት ላይ ይመልከቱ። ይህ ማለት ግን የዓድዋ ድል እና የኣጼ ሚኒሊክ ኣመራር የፈጠረው ትርጉም ወይም የፖለቲካ እንድምታ የለም ለማለት ተፈልጎ ኣይደለም። ኣንዱን ለማጀገን ግን ሃቆች ደፍጥጠን ማለፍ ልማዳችን እንደሆነ ለማስታውስ እንጂ። ሚኒሊክን ለማግዘፍ እና ታሪክን ለመጠቅለል እንዲመች በበፊተኞቹን መሪዎች የተመዘገቡት ድሎች እና ፖለቲካዊ ትግርጉማቸው ሊነገር የማይፈለገው በተራ ስህተት ሳይሆን ሆን ተብሎ በቅጥፈት የሚሰራ እና እየቀጠለ ያለ ጉዳይ ነው። ታሪክ ግን በታሪክነቱ ነው መቀመጥ ያለበት (መጥፎውም ጥሩውም)።

ጸሃፊው እንዳሉት የዓድዋ ድል እውነት ለመላው ጥቁር ሕዝብ ነጻነት ያስገኘ ድል ነበርን? ቀደም ሲል በውጫሌው ውል የተሸጡት ኤርትራዊያንና ግዛቱ በድሉ ማግስት ለባርነት ኣሳልፎ የሚሰጥ ውል እንደገና ኣልተፈረምም!? ራስ መኮነን ይሄንን

የሚያረጋግጥ ደብዳቤ ይዘው ሮም ድረስ መሄዳቸ ይታወቃል። ኣዲስ ኣበባም የማረጋገጫ ውል ተፈርመዋል። ጣይቱ ኣይሆንም ብለው ተቃወሙ እንጂ ትግራይ፣ ሙሉ ዓፋር እና የተወሰነው የሰሜን ጎንደር ኣካባቢም ለጣሊያን ሊሰጡ ወስነው እንደነበር ተጽፈዋል። እዚህ ላይ ከተነሳ ላይቀር ከዓድዋ ጦርነት ጋር ተያይዞ ብዙ ጊዜ የሚነሳው የውጫሌ ውልም የማይታለፍ ችግር ኣለበት። እንደሚታወቀው ወገነተኞቹ የታሪክ ጸሃፊዎቻችን እና የድሉ በዓል በመጣ ቁጥር እየተደጋገመ የሚነሳው የውጫሌ ውል ሌላ ኣንቀጽ የሌለው እስኪመስል ድረስ ኣንቀጽ 17 የጦርነቱ ዋና መንስኤ እንደነበር ሲገለጽ እነሰማለን። ኤርትራን ኣሳልፎ ስለሰጠው የውሉ ኣንቀጽ 3 ግን ኣይነሳም። ሃቁ ግን የጦርነቱ ዋናው መነሻ የጣሊያን ያልተገደበ የቀኝ ኣገዛዝ ፍላጎት (ምስራቅ ኣፍሪካዊ የጣሊያን ኢምፓየር ለመመስረት) እና የኣጼ ሚኒሊክ ስልጣን በጥያቄ ላይ መውደቅ እንደሆነ ግልጽ ሊሆን ይገባል። ስለ ኣገር ቢሆን ኖሮ በተለያዩ ውሎች ኣንድ ከፍለሃገር፣ ረጂም የባህር በርና ህዝቡን በፊርማቸው ኣሳልፈው ባልሰጡ ነበር። ኢትዮጵያ በታሪኺ ለመጀመሪያ ጊዜ መሬቷ እና ህዝቧ ለባእድ (ጣሊያን) በኣጼው ሙሉ ስምምነት ኣሳልፋ የሰጠችበት ጊዜ ነው። "በሚመጡት መንግስታት ተከብሮ የሚኖር" የሚል ሃረግ ያላቸው ኣለም ኣቀፍ ውሎች ፈረሚል።

የተቀሩት ኢትዮጵያዊያንም ቢሆኑ ዓድዋ ላይ ኣውሮፓዊያንን ኣሸንፈው ሲያበቁ በራሳቸው ገዢዎች ኣሳፋሪ የግፍ ኣገዛዝ እና ጭፍጨፋ ውስጥ ገቡ እንጂ ነፃነት ኣላገኙም። በጦርነቱ ማግስት ብቻ እንኳን ብናነሳ ከኣድዋ እስከ ራያ የተፈጸመው ዝርፊያ ፣ ቤት ንብረት ማቃጠል፣ ሴቶች ላይ ኣመጽ እና ጭፍጨፋ እጅግ ዘግናኝ እንደነበር ከጦርነቱ በፊት 20 ኣመታት ኣስቅድሞ የመጣና በጦርነቱ ወቅትም ሬሳ ሳይነሳ ገብቶ ከዓድዋ ጀምሮ እስከ መሃልና ምስራቅ ኢትዮጵያ የተዘዋወረ ብሎም መሳፍንቶቹ እና ንጉሱን ያነጋገረው እንግሊዛዊው ዘጋቢ Augustus B. Wylde በሚያሳዝን ሁኔታ ይገለጽዋል። የሚኒሊክ ወደ ስልጣን መውጣትና የኣድዋ ድል ያመጣው ነገር ቢኖር ኢትዮጵያን እንደ ኣገር ማስቀጠል ብቻ ሳይሆን የኣንድን ብሄር የበላይነት በማንገስ የተቀሩት ብሄሮች መሬት ሀብትና ንብረታቸው በመዝረፍ ብቻ ሳያበቃ ማንነታቸውም ጭምር እንዲከዱ እና ሚኒሊክና መሳፍንቶቻቸው ያመኑበት ብሄር ስም, ባህል እና ቛንቛ ተገድው እንዲያጠልቁ የተደረጉበት በታሪካችን ወስጥ የከፋው ጨለማው ዘመን ነበር የተከተለው። ስለዚህ "የኦሮሞና ሌሎች ሕዝቦችን የጨፈጨፉና ያስጨፈጨፉ ንጉሥ/መሪ ነበሩ" የሚለው ፍጹም የማይካድ ሃቅ ነው። ይህ ለመካድ የሚሞክሩ የሌሎችን ቁስል ደጋግመው ለመጉዳት ከመፈለግ ብቻ የመነጨ ነው። ስለሆነም ይህ በመካከላችን የማይታረቅ ኣስተሳሰብ እና ጥላቻ እየፈጠረ ሄዶ እንዳይበትነን ስጋት ስላለኝ የባሰው ሳይመጣ ከወዲሁ ልናስብበት ይገባል እላለሁ።

ምርጫችን ኣብሮ ለመኖር ከሆነ የሌሎችን ጉዳት ሙሉ እውቅና በምስጠት እና የተፈጸሙት ስህተቶችን ቁልጭ ኣድርጎ በመናገርና በመፃፍ ለመጪው ትውልድ ትምህርት ሰጥቶ ማለፍ ተገቢ ነው። በተቃራኒው፣ ማለትም ኣሁን በምንሄድበት መንገድ መቀጥል ግን ውጤቱ ለማናችንም ኣይበጅም። የጀርመን ናዚዎች በኣይሁዶች እና ኣውሮፓውያን የፈጸሙት ጭፍጨፋ ኣምነው፣ ተጸጽተው እና ይቅርታ ጠይቀው በማለፋቸው እስከ ኣሁን እየተካ የመጣው ትውልድ ደግሞ ያንን ተግባር በግልጽ የሚጠየፍበት ሁኔታ ነው ያለው። በመሆኑም ዛሬ በጀርመን እና በኢስራኤል ያለው ግንኙነትም በጣም ጤነኛ እንደሆነ ይታወቃል። በተቃራኒው ቱርኮች በኣርመኖች ላይ የፈጸሙት ግፍና የዘር ማጥፋት ዘመቻ በመካዳቸው እና እውቅና ባለመስጠታቸው ምክንያት ቂሙ ከርሮ ጉዳዩ ኣሁን በኣለም ኣደባባይ መነጋገሪያ ከመሆኑም በተጨማሪ በሁለቱም ኣገሮች ያለው ግንኙነት ጤነኛ ኣይደለም። ይህ የሚያስተምረን ነገር ቢኖር የኣንዱን ወገን ጉዳት የራስን ህመም ኣድርጎ እውቅና በመስጠት እና ባለመስጠት ምክንያት የሚፈጠር የግንኙነት ልዩነቱ ሰፊ ነው። እውቅና መሰጣጠት እና ይቅር መባባል እሳት ያጠፋል። ሲጀምር ይህ ትውልድ ላለፈው ችግር ተጣያቂ ኣይደለም፣ የሞራል ሃላፊነት ግን ኣለበት። ክህደት ግን ትንሿውንም ነገር ኣግዝፎ ወደ ኣልተፈለገ ሁኔታ ያመራል።

ይሄንን የመሳሰሉ ያገጠጡ እውነታውች ክዶ በታሪካችን ያለመስማማታችን እና የሚያስማማን ብሄራዊ ጀግና ማጣታችን ሊገርመን ኣይገባም። እነዚህ መሪዎች ዕፁብ ድንቅ ነበሩ እያሉ በማሞካሸት የሌሎችን ቁስል መልሶ ማድማት ኣሁን ላለው ያለ መጋባባታችን ዋና ምክንያት ተደርጎ መወሰድ ኣለበት። ስለዚህ "ኢትዮጵያዊ ብሔራዊ ጀግናችን ማን ነው" ለሚለው ጥያቄያቸው ሁላችን የሚያግባባን መልስ ለማግኘት እንችል ዘንድ የተዛባው ታሪካችን ላይ መታረም ያለበት ነገር ስላለ ቅድሚያ እሱ ላይ መስራት ይገባል እላለሁ። መነሻ ሃሳባቸው ግን ሙሉ በሙሉ እጋራለሁ።

ሰናይ ሳምንት!